# ሽንፈት የወለደው ሽፍጥ

## ክፍል አንድ

አዲስ ቶልቻ

ከሁለት አስርት በፊት የደርጉ ባለሟል አሁን ደግሞ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ከፍተኛ አመራር የሆኑት ዶ/ር ኃይሉ ሰሞኑን "ሰማዕታት ቀና ብለው ያዩት የቴሌቪዥንዋን ኢትዮጵያ ነው" በሚል ርዕስ የፓርቲያቸው ልሳን በሆነው ፍኖተ ነፃነት ላይ አንድ ጽሁፍ አስነብበውናል፡፡ የፅሁፋቸው መነሻ አቶ ሴኩቱሬ የኢህአዴግ የውጭ ግንኙነት መምሪያ ኃላፊ ግንቦት 15/2004 ዓ.ም ከሰንደቅ ጋዜጣ ጋር ያደረጉት ቃለምልልስ ነው፡፡

ሴኩቱሬ በቃለምልልሱ "የኢህአዴግ ሰማዕታት ቀና ብለው ቢመለከቱ በተገኘው ውጤት እንደሚደሰቱ እርግጠኛ ነኝ" ብለው ስኬቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ዶ/ር ኃይሉ በፅሁፋቸው ምላሽ የሰጡት እነዚህን ስኬቶች አልቀበልም ብለው ነው፡፡

እኔም አቶ ሴኩቱሬ ከሰንደቅ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለምምልስ የሰጡት ምላሽ ላይ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ትችት ብለው ያቀረቡት ላይ አስተያየት ለመስጠት ወድጃለሁ፡፡ ዶ/ር ኃይሉ ዓርኣያ ሴኩቱሬ "ሰማዕታት ቀና ብለው ቢያዩት እንደሚደሰቱ እርግጠኛ ነኝ" ብለው የጠቀሱዋቸው ስኬቶች የሰነዘሩዋቸውን ትችቶች አንድ በአንድ እንመልከት፡፡

ዶ/ር ኃይሉ ዓርአያ የባለፉት ሁለት አስርት አመታት ስኬት ተደርጎ የተጠቀሰውን የብሄር ብሄረሰብ መብት አስመልክተው "በአሁኑ ግዜ የብሄር ብሔሰቦች መብት ተረጋግጧልን?" ሲሉ በመጠየቅ ይጀምሩና "በወረቀት ላይ ተረጋግጧል፣ በተጨባጭ ግን አልተረጋገጠም" ብለውናል፡፡ ለዚህ አቋማቸው አስረጂ ያሉትን ሃሳብ ሲያቀርቡም፣ "በርካታ የብሄር ብሔረሰቦች ተወካዮች መብታችንን እናስከብራለን በሚል በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች በመታገል ላይ ናቸው" ብለውናል፡፡

በቅድሚያ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ የፓርቲያቸው ፖሊሲ፣ በተለይ የአገሪቱን የፌዴራል መንግስት አወዋቀር የሚመለከተው የኢትዮጵያን ብሔሮችና ብሔረሰቦች በመበጣጠስ በከፋፍለህ ግዛ ስልት መብትና ነፃነታቸው ቀደም ሲል እንደነበሩት አምባገነን ስርአቶች ለአስከፊ ጭቆና የሚያጋልጥ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የብሄር ብሄረሰቦች መብት ተከብሯልም፤ አልተከበረምም በማለት የመተቸት የሞራል ብቃት አላቸው የሚል እምነት የለኝም፡፡

በዚህ በብሄር ብሄረሰብ ጉዳይ ላይ እውነታው ምን እንደሚመስል ከመመልከቴ አስቀድሜ፣ የዶ/ር ኃይሉ አርአያ ፓርቲ አንድነት የብሄር ብሄረሰቦችን መብትና ነፃነት ድራሹን ለማጥፋት የያዘውን ፖሊሲ በአጭሩ ላስታውስ እወዳለሁ፡፡

አንድነት ፓርቲ "የአገሪቱ ፌዴራላዊ አወቃቀር በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን መልክዐምድራዊ መሆን አለበት" የሚል አቋም እንዳለው ሳይሸሽግ በይፋ ሲናገር ቆይቷል፡፡ ይህ ፖሊሲ ተግባራዊ ቢሆን  ቀደም ሲል እንደነበሩት አምባገነን ስርአቶች አንድ ብሄር/ ብሄረሰብ ሁለትና ሶስት ቦታ ተበጣጥሶ በሌሎች ላይ እየተለጠፈ ማንነቱ እንዲቀበር ያደርጋል፡፡

ለምሳሌ በንጉሡ ነግሥቱና በወታደራዊው ደርግ የአምባገነን ስርአቶች አፋርን የሚያክል ትልቅ ብሄር፣ በአንድ በኩል ተቆርጦ ከትግራይ፣ በሌላ በኩል ከኦሮሞ በሌለው ከአማራ ጋር ተበጣጥሶ ተለጥፎ በሁሉም ውስጥ አናሳ በመሆን እንደ ብሄር ያለው ማንነት እንዲቀበር ተደርጎ  እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ የሶማሌ ብሄርም ሁኔታ ተመሳሳይ ነበር፡፡

እንደ ኦሮሞ ያሉ ትላልቅ ብሄሮች ደግሞ ከሌሎች ጋር በሚዋሰኑባቸው አካባቢዎች ተቆራርሰው ከሌሎች ጋር እየተለጠፉ፣ የቀረውንም የተለያየ ብሄራዊ ማንነት ያላቸው ይመስል በተከፋፈለ አስተዳደር ስር እንዲወድቁ ተደርጎ ጠንካራ ብሄራዊ ማንነት እንዳይኖራቸው ተደርጓል፡፡

አንድን ብሄር/ብሄረሰብ ከመበጣጠስና ከመጨፍለቅ በተጨማሪ፣ ሁለትና ሶስት ብሄሮችን/ ብሄረሰቦችን በአንድ የአስተዳደር መዋቅር ስር በማካተት ሁሉም አናሳ ሆነው ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር፣ ቋንቋቸውንና ባህላቸውን የማሳደግ አቅም እንዲያጡ ተደርጓል፡፡ ሁለትና ከዚያ በላይ የተቀላቀሉ ብሄር/ብሄረሰቦች በአንድ መስተዳድር ሥር ሲወድቁ በቋንቋቸው የመስራትና ልጆቻቸውን በቋነቋቸው የማስተማር ዕድላቸው ይጠባል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን የእርስበርስ ግጭት የሚነሳበትም ዕድል ይሰፋል፡፡

በአጠቃላይ አሁን ባለንበት ወቅት የብሄር /ብሄረሰብ መብት አልተከበረም በሚል ለትችት የተነሱት የዶ/ር ኃይሉ አርአያ ፓርቲ ብሄርን በተመለከተ የያዘው ፖሊሲ የኢትዮጵያን ብሄር ብሄረሰቦች ቀደሞ ወደነበሩበት በከፋፍለህ ግዛ መብትና ነፃነታቸውን ወደተነፈጉበት አይነት ስርአት የሚከልስ ነው፡፡

እንግዲህ የእርሳቸው ፓርቲ ፖሊሲ ይህ ሆኖ ሳለ አሁን የብሄሮችና ብሄረሰቦች መብት በወረቀት ላይ እንጂ በተግባር አልተረጋገጠም ብለውናል፡፡ በተግባር መረጋገጡን እንዲያስታውሱት፣ የብሄር/ብሄረሰብ መብትና ነፃነት ምን ማለት እንደሆነ እንመልከት፡፡

ብሄር የራሱ የሆነ ቋንቋና ባሕል ያለው በተመሳሳይ መልክዐምድር የሚኖር አንድ አካል (entity) የሆነ ሕዝብ ነው፡፡ የዚህ ብሄር መብትና ነፃነት መከበር መሠረታዊ መገለጫ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድር መሆኑ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ብሄሩ ባለበት ወሰን ውስጥ ቋንቋውን ለመንግስት የስራ ቋንቋነትና ለማስተማሪያ ቋንቋነት፣ የመጠቀም፣ በባሕሉ መሰረት የመኖር፣ ቋንቋውንና ባሕሉን የማዳበር፣ የክልሉን የተፈጥሮ ሀብት የክልሉን ሕዝብ ተጠቃሚ ማድረግ በሚያስችል አኳኋን መጠቀም የመሳሰሉት መብትና ነፃነቶችን ያካትታል፡፡

አሁን የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች መብትና ነፃነታቸው ተከብረውላቸዋል ወይ? የሚለውን ጉዳይ ለመረዳት ከላይ በአጭሩ ከተጠቀሱት አኳያ መታየት ይኖርበታል፡፡ አሁን የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦች ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ ነው፣ በቋንቋቸው እየሰሩ ነው፣ ልጆቻቸውን በቋንቋቸው እንዲማሩ እያደረጉ ነው፣ የክልላቸው የተፈጥሮ ሃብት ላይ የብሄሩን ተወላጆች ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አኳኋን እያዘዙበት ነው፡፡

ከሁሉ በላይ ደግሞ በሕገመንግስቱ አንቀፅ 39 መሰረት መብትና ነፃነቴ አልተረጋገጠም የሚል ዕምነት ኖሯቸው ጥያቄ ሲያነሱ፣ ጥያቄው የብሄረሰቡ ሕዝብ መሆኑን በሚያረጋግጥ አኳኋን የመገንጠል መብታቸው በዋስትናነት ተቀምጧል፡፡ "የብሄር/ብሄረሰብ መብት አልተከበረም" የሚሉት የዶ/ር ኃይሉ ፓርቲ ይህን ለብሄር ብሄረሰቦች መብት መከበር ዋስትና ይሆን ዘንድ የተቀመጠ "የመገንጠል መብት" አጥብቀው እንደሚቃወሙት ይታወቃል፡፡

ዶ/ር ኃይሉ በፅሁፋቸው የብሄር መብት ተከብሯል አልተከበረም የሚለውን ጉዳይ ከላይ ከተገለፁት ግልፅ ሁኔታዎች አኳያ መከራከሪያ በማቅረብ "አልተከበረም" የሚለውን አቋማቸውን ትክክለኝነት ማሳየትን አልመረጡም፡፡ ይህን በማድረግ "አልተከበረም" የሚለውን በዘፈቀደ የያዙት አቋም ትክክለኛነት ማረጋገጥ ስለማይችሉ ነው የሸሹት፡፡ ለአቋማቸው አስረጅ አድርገው ያቀረቡት " ተከብሮ ከሆነ፣ የብሄር ብሄረሰብ ተወካዮች ለምን መሳሪያ አንስተው ይዋጋሉ?" የሚል ነው፡፡

ለምን እንደሚዋጉ ደግሞ እንመልከት፡፡ ዶ/ር ኃይሉ ጠመንጃ አንስተው ይዋጋሉ ያሉዋቸውን የብሄር "ተወካዮች" ነን ከሚሉት መሃከል ጎልተው የወጡትን የኦሮሞ ነፃነት ግንባር(ኦነግ) እና የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ) በምሳሌነት እንውሰድ፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የኦሮሞና የሱማሌ ብሄሮች ሕዝቦች ሕዝባቸው በሚኖርበት መልክአምድራዊ ወሰን ውስጥ የየራሳቸውን መንግስት መስርተው ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ ይገኛሉ፡፡ የክልላቸው መንግስት በብሄራቸው ቋንቋ - በኦሮሚኛና ሱማሊኛ ነው የሚሰራው፡፡ ልጆች የአፍ መፍቻቸው በሆነ ቋንቋ - ኦሮሚኛና ሱማሊኛ ነው የሚማሩት፡፡ ትክክለኛ ታሪካቸውን እያጠኑ በይፋ የማሳወቅ/ የማስተማር፣ ቋንቋቸውን የላቀ የሥነ ፅሁፍ ቋንቋ መሆን ወደሚችልበት ደረጃ እያሳደጉ፣

ባህላቸውን እየኖሩበትና እያሳደጉት ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ግዜ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ኦሮምኛ በዩኒቨርሲቲዎች በመጀመሪያ፣ በሁለተኛና በሶስተኛ ዲግሪ ደረጃ እንደሚሰጥ ያውቃሉ?

ኦነግና አብነግ ጠመንጃ አንስተው መዋጋትን የመረጡት እንወክለዋለን የሚሉዋቸው የኦሮሞና የሱማሌ ብሄሮች መብቶችና ነፃነቶች ስላልተከበሩ አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ ከሕዝቡ ፍላጎት ውጭ ገንጥለው የሚገዙት ነፃ መንግስት የመመስረት ፍላጎት ስላላቸው የቡድን አምባገነኖች ይህን ለማሳካት የሚያካሂዱት ሙከራ ነው፡፡ እነዚህ ቡድኖች "የትጥቅ ትግል እያካሄድን ነው" ባሉባቸው አመታት ከግዜ ወደግዜ ከጠጨባጭ እውነታው እየተላተሙ፣ ከሕዝብ ልብ ይበልጥ እየራቁ፣ ስማቸው ብቻ ቀርቶ ለኦሮሞም ሆነ ለሱማሌ ብሄሮች ሕዝብ መብትና ነፃነት ቅንጣት ታክል ደንታ የሌለውና ዋነኛ አላማው ፌዴራላዊት ኢትዮጵያን ማፈራረስ ብቻ የሆነው ሻዕቢያ ላይ ተለጥፈው የማተራመስ ተልእኮውን ለማስፈፀም የሚባዝኑ ጥቂቶችን ያቀፉ አናሳ ቡድን ለመሆን የበቁትም ለዚህ ነው፡፡

በአሁኑ ግዜ የኦሮሞ፣ የሱማሌም ሆነ ሌሎች ብሄሮችና-ብሄረሰቦች መገንጠል በራሱ መብትና ነፃነት ወደተከበረበት ሁኔታ የሚያሸጋግር አንድና ብቸኛ አማራጭ አለመሆኑን ጠንቅቀው ተገንዝበዋል፡፡ በጋራ የሚኖሩበት መብትና ነፃነታቸው የተከበረበት ስርዓት መመስረት ከቻሉ፣ አብሮ መኖሩ የተሻለ መሆኑን ያውቁታል፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ መንግስም ይህንን በተግባር አረጋግጧል፡፡ "ምናልባት መብትና ነፃነቴ የሚታፈንበት ሁኔታ ቢፈጠርስ?" የሚል ስጋት እንዳያድርባቸው በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 39 ዋስትና ተሰጥቷቸዋል፡፡

እናም ኢትዮጵያ ውስጥ የብሄር ጭቆና አለ የሚለውን ለማሳየት በዶ/ር ኃይሉ አርአያ በአስረጂነት የቀረበው ሃሳብ ከንቱና ሚዛን የማይደፋ የመቃወም አባዜያቸውን ለመግለፅ ብቻ የቀረበ ነው፡፡

አቶ ሴኩቱሬ "አገራችን ዴሞክራሲያዊ ሆናለች" በሚል ያቀረቡትን ያለፉ ሁለት አስርት አመታት ስኬቶችም ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ሊተቹት ሞክረዋል፡፡ዶ/ር ኃይሉ "አሁን በአገራችን ዴሞክራሲ የለም" ባይ ናቸው፡፡ ለዚህ አቋማቸው መከራከሪያነት ያቀረቡት "ፓርላማው 99.6 በመቶ በአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ስር ወድቋል፣ ፕሬስና ሲቪክ ማህበራቱም በአሳሪ ሕጎች ተጠፍረዋል፣ ሕዝብ በፀረሽብርተኝነት ሕግ በፍርሃት ድባብ ውስጥ ተውጧል" የሚል ሃሳብ ነው፡፡

ሁላችንም እንደምናውቀው የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ከጸደቀ በኋላ በአገሪቱ በተካሄደ አራት ምርጫዎች ላይ፣ በደርግ የስልጣን ዘመን በ1979 ዓ/ም ዶ/ር ኃይሉ ተመረጡ ተብለው አባል ከነበሩበት የደርግ ብሄራዊ ሸንጎ ምርጫ ላይ ከነበረው ፍፁም በተለየ ሁኔታ በርካታ ፓርቲዎች በነፃነት ተደራጅተው በይፋ ለምርጫ ፉክክር ቀርበዋል፡፡ በርካታ ፓርቲዎች ያለምንም ገደብ ለፉክክር መቅረብ የቻሉበት ሁኔታ ቀዳሚው የዴሞክራሲ መገለጫ ነው፡፡

2002 ዓ/ም በተካሄደው 4ኛ ዙር ምረጫ ከፍተኛው የመንግስት የሥልጣን አካል በሆነው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ውስጥ ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ 99.6 መቀመጫዎችን ማሸነፉ እርግጥ ነው፡፡

ኢሕአዲግ 99.6 በመቶ ያሸነፈበት የ2002 ምርጫ እስከ ድምፅ መስጫው እለት የነበረው ሂደት፣ የአገር ውስጥም ሆነ የውጥ ታዛቢዎች እንደመሰከሩት በአፍሪካ ታይቶ የማይታወቅ ዴሞክራሲያዊ ነበር፡፡ የዶ/ር ኃይሉም ፓርቲ በዚህ ላይ አንድም በተጫባጭ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ የሂደቱን ዴሞክራሲያዊ ያለመሆን የሚያሳይ መከራከሪያ አቅርቦ አያውቅም፣ አሁንም ማቅረብ አይችልም፡፡

የምርጫ ውጤት ዴሞክራሲያዊ ነው ወይንም አይደለም የሚባለው አንድ ፓርቲ በከፍተኛ አብላጫ ድምፅ በመመረጡ ሊያም በርካታ ፓርቲዎች የህዝብ ድምፅ በመከፈላቸው ሳይሆን፣ ሕዝቡ የሠጠው ድምፅ በትክክል በመከበሩ ነው፡፡ እናም በ2002 ዓ/ም በተካሄደው ምርጫ አሁን በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ የ99.6 በመቶ የሕዝብን ድምፅ አግኝቷል፡፡ ምርጫው ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ይህ የሕዝብ ድምፅ መከበር ነበረበት፡፡

ፓርቲዎች ተመካክረው ሕዝብ የሰጠውን ድምፅ ወደጎን ትተው፣ "አንተ ይህን ያህል፣ አንተ ደግሞ ይህን ያህል የም/ቤቱ መቀመጫ ይኑርህ" ተባብለው ስልጣን ቢቀራመቱ ዋነኛ የዴሞክራሲ መገለጫ የሆነውን የሕዝብን ብቸኛ የመንግስት ስልጣን ምንጭነትና ባለቤትንትን ሸረዋል፡፡ በመሆኑም የሥልጣን ድልድሉ ዴሞክራሲያዊ አይሆንም፡፡ ዶ/ር ኃይሉ ምርጫውን ዴሞክራሲያዊ አይደለም የሚል እምነት ካላቸው፣ ሕዝብ በይህን ያህል መጠን አንድን ፓርቲ ሊደግፍ እንዴት ይችላል? ከሚል ምናባዊ መላምት ተላቀው፣ በተጨባጭ የተነፈጉትን ወይም ሌላው ወገን ያልአግባብ የወሰደውን የሕዝብ ድምፅ ማሳየት ነው፡፡ እስከዛሬ ፓርቲያቸውም እርሳቸውም ከምናባዊ መላምት ውጭ ይህንን አድርገው አያውቁም፡፡

ሩቅ ሳይሄዱ ፓርቲያቸው አንድነት የጋራ መድረክ ከፈጠረበት የፖለቲካ ድርጅት ማለትም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) ጋር በአንድ ምልክት በ2002 በተካሄደው 4ኛ ዙር ምርጫ የቀረቡበትን ሁኔታ መለስ በለው ቢያስታውሱ፣ፓርቲያቸው ለምን የህዝብ ድምፅ ሊያጣ እንደቻለ በግልፅ ያሳውቃቸዋል ብዬ አምናለሁ፡፡

እንደሚታወቀው በመድረክ ስር የተሰባሰቡ ፓርቲዎች ፍፁም የተለያየ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች የሚያራምዱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንድነት "የሊበራል ዴሞክራሲ መርህ ተከታይ ነኝ፣ መሬት የሚሸጥ የሚለወጥ የግል ሃብት መሆን አለበት" የሚል አቋም ሲያራምድ፣ ሕብረትና ኦሕኮ በተቃራኒው "ሶሻል ዴሞክራት ነን፣ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የሕዝብ ሃብት ነው" የሚል አቋም አራማጆች ናቸው፡፡ የአገሪቱን ፌደራላዊ አወቃቀር በተመለከተ፣ አንድነት መዋቅሩ መልከዐ ምድራዊ መሆን አለበት ሲል፣ ሕብረት፣ ኦሕኮ፣ አፌዴንና ሌሎችም በብሄር ላይ የተመሰረተ ፌደራላዊ አወቃቀር የሚያራምዱ ናቸው፡፡

እነዚህ በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ፍፁም ተቃራኒ አቋም ያላቸው ፓርቲዎች በ20002 የተካሄደው 4ኛ ዙር ምርጫ ላይ በአንድ የምርጫ ምልክት ሲቀርቡ፣ ቀደም ሲል በተናጥል ይደግፏቸው የነበሩት፣ አስከትለውት የመጡትን እያሰቡ ድምፃቸውን ለመስጠት ተቸገሩ፡፡ እናም ድምፃቸውን ነፈጉዋቸው፡፡ በዚህም ሳቢያ ከመደጋገፍ ይልቅ ተያይዘው ወደቁ፡፡ ይህ ሁኔታ በ3ኛው ዙር የመንግስት የስልጣን ዘመን የምክር ቤት መቀመጫ የነበራቸው የመድረክ ፓርቲዎች እንዲሸነፉ በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡ የሽንፈታቸው አንዱ መነሻም ይኸው  በውስጣቸው ያለ ግልጽ ልዩነትና ተጻራሪ አቋም እንደነበር መረዳት አያዳግትም፡፡